# አጭር ቆይታ ከፌዮደር ዳስተዬቭስኪ ጋር

ታላቁ የራሽያ ደራሲ ፌዮደር ዳስተዬቭስኪ በዓለም ከታወቀባቸው ስራዎቹ ፤ "Crime and punishment" "Idiot" ...ወዘተ ከመሳሰሉት ጋር "The Devils" ወይም "The Possessed" የተባለው ፖለቲካ ነክ ድርሰት ወይም ፖለቲካል ኖቭል አንዱ ምርጥና ታዋቂ ድርሰቱ ነው;; በዚህም ስራው ዳስተዬቭስኪ በወቅቱ የግዜውን ታሪካዊና ፖለካዊ የራሽያ እውነታ በምናቡ መስተዋት ለመዳሰስና ለማንፀባረቅ የሞከረበት ሲሆን እንደራሱም አገላለጽ በ1873 በተጻጻፈው የግል ደብዳቤው ላይ "'The Devils' is almost historical sketch to explain the monstrosities and situation in Russian life." ብሎ ነበር;;

በዚህ ድርሰቱ ዳስተዬቭስኪ ብዕሩ ያነጣጠረው የዘመኑን የራሽያ ልሂቃን ወይም ምሁራን ሁለት ተከታታይ ትውልዶች /Intellectual generations/ ላይ ሲሆን በእነኚህ ሁለት ትውልዶች መሀከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በውስጣቸውም የተከሰቱትን የመስመር ልዩነቶች መንስኤና አንዱ ትውልድ በሌላው ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ የሚመረምርበትና በድርሰት ክህሎቱ አጉልቶ የሚያሳይበት ነው;;

በወቅቱ የመጀመሪያው ቀዳሚው ትውልድ "liberals" "westernizers" ተብሎ የሚጠራው ሲሆን ተከታዩ ሁለተኛው ትውልድ ደግሞ "Nihilist" "Anarchist" "Terrorist" በመባል የሚታወቀውና ዳስተዬቭስኪ "Devils" "Demons" (አጋንንት፤ ሰይጣናት፤ዲያቢሎሶች፤ ክፉ መናፍስት) እያለ የሚጠራው ክፍለ ትውልድ ነው;; መፅሐፉም ስያሜውን ያገኘው ከዚሁ ሲሆን የዚህን ትውልድ እኩይ ተግባራት ስነ ልቡናዊ ክስተት (psico-phenomen) በገፀ ባህርይ ቀርፆ ደምና ስጋን አላብሶ የሚያስነብብ ጠቢባዊ ስራ ነው;;

ይህ የዳስተዬቭስኪ መጽሀፍ የሚያስጭብጠው አብይ ቁምነገርና የመልዕክቱ መቋጫ ነጥብ የቀዳሚው ትውልድ liberals/westernizers አባት ትውልድ የአስተሳሰብና የግብር ደካማነት፤ ፍሬ አልባነትና መሃንነት በቀጣዩ ትውልድ ለተከሰተው የአጥፍተህ ጥፋ ጭፍን ተቃዋሚነት /Nihilism/ ፤ ስርአተ-አልበኝነትና ሽብርተኝነት መሰረት ብቻ ሳይሆን ሎጂካል መደምደሚያው እንደሆነ የሚጠቁም ነው;; "The liberalism/westernism of the first without any aim and incapability of deeds inevitably gave birth to absolute negation of all by the next" ይለዋል;;

የዚህ ፅሁፍ ዓላማም ይህንን ዳስተዬቭስኪ በዘመኑ ያንጠረጠረውን ፍሬሃሳብ መሰረት በማድረግ ከኛ ህብረተሰብ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ክስተት ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን ብሎ ለመጠየቅና ካለውስ የመሳ ለመሳ ተመሳሳይነቱ ወይም ጣምራነቱ /parallel/ ምን ዓይነት መልክ ሊኖረው እነደሚችል ለመዳሰስ ይሆናል;; መቼም ዛሬ የምናየውን የኢትዮጵያን ዲያስፖራ የጥላቻና የጥፋት ፖለቲካ /Nihilism/ የተመለከተ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሰው ይሄ ክፉ መንፈስ ከየት ተፈጠረ? እንዴትስ ሊከሰት በቃ? ብሎ መጠየቁ አይቀርም;; ለስማዩም

ለምድሩም ህግ ማደር የተሳነው፤ /common sense ወይም conventional wisdom የማይገራው የስይጠና ፖለቲካ ምን አመጣው ብሎ ለጥያቄ መነሳሳቱ አይቀርም;;

ይህ "The Devils" ወይም "The Possessed" የተሰኘው የዳስተዬቭስኪ ስራም ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ መንደርደሪያ በመሆን የዲያስፖራውን ፖለቲካ ከተለየ ማዕዘን እንድናየውና እንድንመረምረው ይጋብዛል;; ለተለየ አሳቦቶችም ትራስ በመሆን አዳዲስ ሃሳቦችን ያስጭራል;; ከጊዜያዊና ወቅታዊ የዲያስፖራው ሆያሆዬና አስረሽ ምቺው ትንተና ወጣ ብለንም ጉዳዩን በሰፊ ታሪካዊና ሰነ ልቡናዊ ማቀፊያ /context/ ውስጥ እንድንቃኘው ይመራል;; ከሶስት እስከ አምስት ፐርሰንት የማይበልጠውን የዲያስፖራው ፖለቲካ ጥጥ ፈታዮች ፤ ደዋሪዎችና ሸማኔዎች ውስጣዊ ስነ-ልቡና /psychology/ በዳስተዬቭስኪ ዓይንና መነፅር እንድናየውም ያደርጋል;; የዚህን "የአብዮቱ ልጆች" ትውልድ ከፉ መንፈስ የመነሻና መድረሻ አቅጣጫውን በኮምፓስነት ሊጠቁመን ያስችል ይሆናል;;

እንደምናውቀው ዘመናዊ ትምህርት ኢትዮጵያ ከገባበት ግዜ አንስቶ የኢትዮጵያ ምሁራን/ልሂቃን በሁለት ተከታታይ ትውልዶች የሚከፈል ነው;; ( ሶስተኛው ትውልድ ባሁኑ ወቅት ፊታችን እየተወለደና በዓይናችን ስር እያቆጠቆጠ የሚገኝ ሲሆን እሱን ወደ ኋላ የምመለስበት ርዕስ ይሆናል ) እነኚህ የቀድሞውና ያሁኑ ሁለት የኢትዮጵያው ትውልድ ከዳስተዬቭስኪ ዘመን የራሽያ ልሂቃን ትውልዶች ጋር በቅርጽም ሆነ በይዘት በዓይነትም ሆነ በጥራት ያለው ሰፊ የትዬለሌ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሂደታዊ ተፈጥሮው አንፃራዊ ተመሳሳይነትና ታሪካዊ ጥምረት /parallel, analogy/ እነዳለው መገመት ብዙ አያዳግትም;; የዚህም መሰረቱ ሁለቱ አገሮች የነበሩበት ማህበራዊ ስርአትና ከምዕራቡ ዓለም ስልጣኔ ጋር ያላቸው መስተጋብር አዲስነት ያመሳስላቸዋል;;

ለማስታወስ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ልሂቃን ትውልድ "ጃፓናይዝረስ" ተብለው
ከሚጠሩት አንስቶ እስከ አብዮቱ መባቻ ድረስ ያሉትና በዘመናዊ ትምህርትና በጥገናዊ ለውጥ ኢትዮጵያን ለስልጣኔ ማብቃት ይቻላል የሚል መስመር ሲከተሉ የነበሩት ሲሆኑ ሁለተኛው ትውልድ ደግሞ "አብዮታውያን" ከአብዮቱ መባቻ እስከ አሁን ያለው ነውጠኛውን ትውልድ የሚጠቀልል ነው;; አዲሱን ሶስተኛው ትውልድ ወደ ኋላ እመለስበታለሁ;;

ወደ መጽሀፉ ስንመለስ የዳስተዬቭስኪ "The Devils" ታሪክ የሚከናወነው በራሽያ አንዲት ምናባዊ የክፍለ ሀገር ትንሽ የግዞት ከተማ ውስጥ ሲሆን በዘመኑ ንጉሳዊ ፊላጭ ቆራጭ ስርዓት በሰፈነባት ሩስያ ገፀ ባህርያቱም ከዚሁ ህብረተሰብ ማህበራዊ ክፍል የተወጣጡ ሆነው እናገኛቸዋለን;;

ዳስተዬቭስኪ የመጀመሪያው ትውልድ ተወካይ ወይም ናሙና አድርጎ የሳለው ገፀ ባህርይ ስቴፓን ትራፌሞቪች የሚባሉ ፕሮፌሰር ሲሆኑ እሳቸውም ሊበራል ... ዌስተርናይዘር ... ጀግንነት የሚቃጣቸው ግን በራሳቸው ጥላ የሚደነብሩ ... ሁሉን አዋቂና ደግሞ እምቦቀቅል ... ራሳቸውን በመስታወት ባዩ ቁጥር አገር ወዳድነቱ የሚበረታባቸው ...

ግን ፈሪሃ ግዜሩ ያለባቸው አስቂኝም አሳዛኝም ገፀ ባህርይ ሆነው እናገኛቸዋለን;; የራሽያ ሊትሬቸር አዋቂና ተመራማሪ ፕሮፌሰር ቢን የስቴፓን ትራፊሞቪችን ገፀ ባህርይ እንደሚከተለው ይገልፀዋል;- "... Stephan Trofimovich fancies himself a "progressive patriot", a "picturesque public character" living in "exile" ... He moves through a number of mutations: the liberals as dependent, the liberal as infant, the liberal as fool (in both senses), the liberal as dandy, the liberal who tries to assert his independence, the liberal as spoiled darling of the radicals, as agent provocateur, as provincial, as bohemian, as bootlicker of authority, and the liberal as philosopher"

ስቴፓን ትራፊሞቪች ከላይ በተጠቀሱት በእያንዳንዱ ተለዋዋጭ የገፀ ባህሪይ ሚናቸው ዳስተዬቭስኪ ለማስረዳትና ለማስጨበጥ የሚፈልገው ሃቅ "The higher liberalism/westernism and the higher liberal, that is liberal without any definite aim, are possible only in Russia" የሚለውን የራሱን አባባል ነው;;

... His (Stepan Trofimovich) phantasmagorical wanderings inevitably recall Don Quixote, and indeed he becomes a Russian Quixote seeking truth, love and reality." ይለዋል;;

ስቴፓን ትራፌሞቪች ከሌሎች ገፀ ባህርያት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ትርጉም በሚመለከት ፕሮፌሰር ቢን እንዲህ ይገልፀዋል፡- "In the relationship between

Stepan Trofimovich and Varvara Petrovna (an eccentric land owner) Dostoevsky seems to suggest the relationship between matriarchal Russia and her errant liberalism/westernism ... by making Stepan Trofimovich protégé of Varvara Petrovna Dostoevsky destroys the liberals/westerners claim to intellectual independence ... by making him the parent of peter ( Nihilist, control of the book) he implies that nihilism is the necessary outcome of liberalism/westernism.

በአሁኑ ግዜ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ትውልድ በአብዛኛው በውጭ አገር በ"exile" ስር ስዶ የሚኖር ሲሆን በጣሊያን ወረራ ምክንያት የጀመረውን የውጭ ኑሮ በኋላም እስካሁን ልዩ ወግና ማዕረግ ተደርጎ ሊቆጠር የበቃውን የስደት ባህል ያስፋፋው ይሄው ክፍል ነው;; የዚህ ትውልድ አዛውንቶችም አሁን ድረስ ራሳቸውን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓትርያርክና ጳጳሳት አድርገው የሚቆጠሩና የነሱን ምክር ያልጠየቀና እነሱ ያልባረኩት ፖለቲካ ሁሉ ውጉዝ በኩሉ ዓለም ብለው የሚኮንኑ የዲያስፖራው ፖለቲካ ነፍስ አባቶች ናቸው;;

የመጽሀፉ ዋንኛ ተዋናይና ዳስተዬቭስኪ "Devils" እያለ የሚጠራው ሁለተኛ ትውልድ ተወካይ አድርጎ የቀረፀው ገፀ ባህርይ ፒተርንና የሱን ቡድን ወይም የ"ድርጅት ሴል" አባላት

ሲሆን ፒተር የዳስተዬቭስኪ ትልቁ ዲያቢሎስና የኛው ዲያስፖራ ፖለቲከኛ ሙሉ ምስል ነፀብራቅ /mirror reflection/ ነው፡፡

የፒተርን ምግባር ማዕከላዊ ስልት ሊቁ እንዲህ ይገልጹታል፤-"Peter controls the language, the conversation and in this way controls the people. He backs it up with force however."

በመቀጠልም "... In order to act one must have a text to believe in and Peter is the producer of texts. However it seems that Peter himself has no text except to make up texts and then control them. He is a master of finding out texts for which the characters already have created for themselves, then changing, manipulating the text induce the character to act in a way which he wants them to. Part of it, is convincing them that he knows everything and everyone and what everyone thinks - and this becomes the textual spider web in which every one is caught."

ይህ በርግጥ የዲያስፖራው ፖለቲከኛ የግብር ፎርሙላ ነው፡፡ ልክ እንደፒተር ሁሉ የዲያስፖራው ፖለቲከኛ ሁሉን አዋቂ (infallible, semi-God, God-manhood) ና text /theory/ ቀማሪ ነው፡፡ የራሱ የሆነ text ግን የለውም፡፡ ማለትም የራሱ የሆነ ራዕይ ህልም /vision/ የለውም፡፡ ሰዎች ሁሉ የሚያውቁትን text ለውጠ ገለባበጦ እሱ በፈለገው መልኩ ይተረጉመዋል፡፡ ቀጥሎም እሱ በሚቆጣጠረው መንገድ ሰዎችን ለድርጊት ያሰማራል፡፡

ለምሳሌ የዲያስፖራው ፖለቲከኛ ተወዳጅ text መሃከል "ዲሞክራሲ" አንዱ ነው፡፡ ፡ የዲሞክራሲ መብትና ነፃነት ፤ የዲሞክራሲ ምርጫ ፤ የመናገርና የመፃፍ ሃሳብን በነፃነት የማነሸራሸር ፤ ወዘተ የሚሉት ጽንሰ ሃሳቦች ዲያስፖራው ቀን ከሌት የሚምል የሚገዘትባቸው ቃለ ወንጌሉ ናቸው፡፡ ግን ሁሉም እነደሚያውቀው ... አደለም በአገር ደረጃ ባለ የፖለቲካ መድረክ ላይ... በራሱ ውስጥ "ድርጅት" በሚለው ጣራ ስር ልዩነቶችን እነዴት እነደሚያስተናግድ ለሁሉም ያደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ለየት ያሉ ድምጾች /decent voices/ እነዴት እነደሚረሸኑ አየተናል ሰምተናል፡፡ ለግዜው የዛሬው የሃኬትና የስድብ ጥይቱን ነገ ቢሆንለት በመዳብ ጥይት እነደሚተካው ግን ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በዚህ የኛዎቹ የዳስተዬቭስኪን ፒተር በእጥፍ ያስከነዱታል፡፡

ለዲያስፖራው ፖለቲከኛ "ዲሞክራሲ" ማለት የሱ ሃሳብ በቻ የሚስተናገድበት መድረክ ፤ እሱ ብቻ የሚመረጥበት ምርጫ ፤ በእድር ዳኝነት ሁሉን ለሁሉም እሱ ብቻ የሚያውቅበትና የሚፈርድበት ችሎት ማለት ነው፡፡

ሌላው የዲያስፖራው ፖለቲከኛ ተፈቃሪ text "የአገር አንድነት" ነው;; ስለ አገር አንድነትና ልዑላዊነት ጠበቃም ሆኖ ይከራከራል አቃቤ ህግም ሆኖ ይወነጅላል;; ነገር ግን በዓለም ላይ የመጀመሪያው አንድ ቁጥር የኢትዮጵያ አንድነት ጠላት ከሆነውና የመቶ ዓመት አጀንዳ ካለው ከኢሰያስና እነዲሁም ከኦነግና ከሌሎች ጋር ለመቀናጀት ምንም ችግር የለበትም;; ምነው ?!...ለምን?! ሲባል መልሱ "የፖለቲካ ጥበብ" ነው ይላል ....'ግዴላችሁም እኔ ሁሉን አውቃለሁ' እያለ ባንድ ዓይኑ የሚጥቀስ ይመስላል! ...text manipulate ማድረግና 180 ድግሪ ገልብጦ ለራስ ዓላማ ማዋል ማለት ይህ ነው;; ልዑላዊነትን ለፈረንጅ አሳለፎ ለመስጠት የውጪ ፓርላማ ደጅ በመጥናት ለአገርና ለሕዝብ መዓት በመመኘት የ"አገር ፍቅር" ትርጉምን ገልብጦ በጭንቅላቱ ሲያቆም ዓይኑ አይረግብበትም;;

ግን ለምን? ለምንድነው ዲያስፖራው ይህን ሁሉ እንዲህ የሚያደርገው? እውነትና ሃሰት ተማተውበት ነው? ለዲያስፖራው ፖለቲከኛ እውነት ማለት ምን ማለት ነው? ለድርጊቱ ሁሉ መሪ ምክንያትና ምንጩ /motive/ ምንድነው? ... ሥልጣን? ...ሥልጣን ከሆነስ ሥልጣን ምን ያደርግለታል? ሥልጣንስ እንዲፈልግ ያስገደደው መሰረታዊ ምክንያት አለ? ካለ ምንድነው? ...ዲሞክራሲ ለማስፈን ወይም ለአገርና ለህዝብ ጉዳይ ካልሆነ ለምንድነው ስልጣን የሚፈልገው የሚመኘው የሚጠማው? ...ስልጣን ለመፈለግ ወይም የመፈለግ የራሱ ፍልስፍና ይኖረው ይሆን? ዳስተዬቭስኪ ለሱ Devils መልስ አለው? ለእኛዎቹስ ይሰራ ይሆን?

**ይቀጥላል**